- እግዚአብሔር ለፈርዖን ለግብፃውያንና ለእስራኤላውያን እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑንና ሌላ አምላክ አለመኖሩን ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ነበር።

- ከእነዚህ አስፈሪ መቅሰፍቶች በኋላም እንኳ ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ አልፈለገም ነበር።

- ከእነዚህ አስፈሪ መቅሰፍቶች በኋላም እንኳ ፈርዖን እግዚአብሔርን መታዘዝ አልፈለገም ነበር።

- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ሊያሸንፈው ይችላል?
- አይችልም።

- ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ሊያሸንፈው ይችላል?
- አይችልም።

- ከእግዚአብሔር ጋር በሚታገሉት ላይ ምን ይደርስባቸዋል?

- እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል።

- በሚቀጥለው ትምህርት የመጨረሻውን መቅሰፍት እንመለከታለን።



ትምህርት 28

1. ሙሴ ሲነድድ ያየው ቁጥቋጦ ያልተቃጠለው ለምንድን ነው?
ሀ- ምክንያቱም በቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር ስለ ነበር ነው።

2. እግዚአብሔር በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ የነበረው ለምንድን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ቁጥቋጦ ውስጥ የነበረው ስለ እስራኤላውያን ከሙሴ ጋር ለመነጋገር ፈልጎ ነው።

3. የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ከእስራኤላውያን ጋር የሚመሳሰለው በምንድን ነው?
ሀ- እሳቱ ቁጥቋጦውን ሊያጠፋ እንደ ፈለገ ሁሉ ሰይጣንና ፈርዖንም እስራኤላውያንን ለማጥፋት በመፈልጋቸው ነው።
ለ- እግዚአብሔር በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ እንደ ነበረ ሁሉ ከእስራኤላውያንም ጋር በመሆኑ ነው።

4. ያለና የሚኖር» የተሰኘው የእግዚአብሔር ስም ትርጉሙ ምንድን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም ማለት ነው።
ለ- እግዚአብሔር መጨረሻ የለውም ማለት ነው።
ሐ- እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይኖራል ማለት ነው።
መ- እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ፈጽሞ የለም ማለት ነው።

5. እስራኤላውያንን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ ፈርዖን እንደማይፈቅድ እግዚአብሔር ያውቃል?
ሀ- አዎን። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል።

6. እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር አውጥቶ እንዲመራ የመረጠው መሆኑን የሚያሳየው የመጀመሪያ ምልክት ምን ነበር?

ሀ- የሙሴ በትር ወደ እባብነት መለወጥና ተመልሳ በትር መሆን።

7. እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ እንዲያወጣቸው፥ መምረጡን የሚያሳየው ሁለተኛው ምልክት ምን ነበር?

ሀ- ሙሴ እጁን በብብቱ ውስጥ አስገብቶ ሲያወጣው እጁ ለምፃም መሆኑና፤ መልሶም በብብቱ ውስጥ ሲያስገባው እጁ ጤናማ መሆኑ ነው።

8. እግዚአብሔር ሙሴ ወደ ፈርዖን ሲሄድ እንዲረዳው የላከው ማንን ነበር?

ሀ- የሙሴን ወንድም አሮንን።

9. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት ለማውጣት የፈለገው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ስለ ወደዳቸውና በባርነት እንዲኖሩ ስላልፈለገ ነበር።

ለ- እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮቹን ወደ ከነዓን እንደሚመልስ ቃል ገብቶ ስለ ነበር ነው።

ሐ- እግዚአብሔር ለአብርሃም ከዘሮቹ ከእስራኤላውያን አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገብቶ ስለ ነበር ነው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ የገባውን ቃል በመጠበቅ፥ ወንድሙ አሮንን እንዲረዳው ላከለት።

ዘጸአት 4፡27-28

27- እግዚአብሔር አሮንን፣ «ሙሴን እንድታገኘው ወደ ምድረበዳ ሂድ» አለው። እርሱም ሙሴን በእግዚአብሔር ተራራ አገኘው፣ ሳመውም።

28- ሙሴም እግዚአብሔር እንዲናገር የላከውን ቃል በሙሉና እንዲፈጽማቸው ስላዘዘው ተአምራዊ ምልክቶች ሁሉ ለአሮን ነገረው።



ዘጸአት 10፡21-23

21- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «በግብፅ ላይ ድቅድቅ ጨለማ እንዲወርድ እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ» አለው።

22- ሙሴም እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፤ በመላው ግብፅ ላይ ለሦስት ቀናት ድቅድቅ ያለ ጨለማ ሆነ።

23- በእነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ አንዱ ሌላውን ማየት ወይም ከነበረበት ቦታ መንቀሳቀስ አይችልም ነበር። ይሁን እንጂ እስራኤላውያን በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ ብርሃን ነበር።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቀምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- እግዚአብሔር መቅሰፍቱን በላከ ቁጥር ሁሉ ፈርዖን ምን ይል ነበር?

- ፈርዖን እስራኤላውያንን እንደሚለቅ ለሙሴ ይነግረው ነበር።

- እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ባቆመ ቁጥር ፈርዖን ምን ይል ነበር?

- ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም ይል ነበር።

- መቅሰፍቱ፥ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ያልገባው ለምንድን ነው?

- ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ እግዚአብሔር እነርሱን እንደሚባርካቸውና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

በሉ።

- መቅሰፍቱ፥ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 10፡13-15

13- ስለዚህ ሙሴ በግብፅ አገር ላይ በትሩን ዘረጋ፤ እግዚአብሔርም በዚያን ቀንና ሌሊት በሙሉ በምድሪቱ ላይ የምሥራቅ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ፤ በማግሥቱም ነፋሱ አንበጣዎቹን አመጣ።

14- እነርሱም ግብፅን በሙሉ ወረሩ፤ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሆነው የአገሪቱን ዳር ድንበር ሁሉ አለበሱ። እንዲህ ያለ የአንበጣ መዓት ከዚህ ቀደም አልነበረም፣ ወደፊትም ደግሞ አይኖርም።

15- ምድሩ ሁሉ ጠቁሮ እስኪጨልም ድረስ አለበሱት። ከበረዶ የተረፈውን በመስክ ላይ የበቀለውንና በዛፍ ላይ ያለውን ፍሬ ሁሉ፣ ጠርገው በሉ። በግብፅ ምድር ሁሉ በዛፍ ላይ ወይም በተክል ላይ አንዳች ቅጠል አልተረፈም ነበር።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በዘጠነኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የጨለማ መቅሰፍት ላከ።

- ጨለማ ለሦስት ሙሉ ቀን የፈርዖንና የግብፃውያንን ምድር ሸፈነ።

- መቅሰፍቱ፥ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።



- ከዚያም ሙሴና አሮን ወደ ግብፅ ተጓዙ።

- ሙሴና አሮን ግብፅ እንደ ደረሱ እስራኤላውያንን በአንድ ላይ ሰብስበው እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ሁሉ ነገሯቸው።

ዘጸአት 4፡29-31

29- ሙሴና አሮን ሄዱና የእስራኤልን ሕዝብ አለቆች በአንድነት ሰበሰቡ፤

30- አሮንም እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ቃል በሙሉ ነገራቸው። ተአምራቱንም በሕዝቡ ፊት አደረገ።

31- ሕዝቡም አመኑ። እግዚአብሔር ስለ እነርሱ የሚገደው መሆኑንና መከራቸውን ማየቱን በሰሙ ጊዜ፣ ተንበረከኩና በስግደት አመለኩት።

- እስራኤላውያን በሙሴ በኩል የተነገራቸውን የእግዚአብሔርን ቃል አምነዋል?

- አዎን።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ማመናቸው ጥሩ የሆነው ለምንድን ነበር?

- እስራኤላውያንን ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ስለነበር።

- እስራኤላውያንን ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሰለነበር።

- የእግዚአብሔርን ቃል ካላመንን፥ እግዚአብሔርን ምን እያልነው ነው?

- ውሸታም።

- እግዚአብሔር በቃሉ የማያምኑትን ያድናቸዋል?

- አያድናቸውም።
- የእግዚአብሔርን ቃል የማናምን ከሆነ መዳን አንችልም።
- እግዚአብሔር ለመዳን በቃሉ እንድታምኑ ይፈልጋል።

- እኛን ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- እኛን ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

- ሙሴና አሮን ከእስራኤላውያን ጋር የሚያደርጉትን ንግግር ካበቁ በኋላ ከፈርዖን ጋር ለመነጋገር ሄዱ።

ዘጸአት 5፡1-2

1- ከዚህ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው፣ «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር “በምድረ በዳ በዓል እንዲያደርግልኝ ሕዝቤን ልቀቅ” ይላል» አሉት።

2- ፈርዖንም፣ «እንድታዘዘውና እስራኤልን እንድለቅለት ለመሆኑ ይህ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፣ እስራኤልንም አልለቅም» አለ።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዲለቅ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሙሴ ሲነግረው ምን አለ?

- ፈርዖንም «እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም» አለ።

- ፈርዖን እግዚአብሔርን ያላወቀው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ፈርዖን እግዚአብሔርን ለማወቅ ባለመፈለጉ ነው።



•

- ከባድ በረዶ በመላው ግብፅ ወረደ፤ የፈርዖንንና የግብፃውያንን ዛፎችና እህሎች በሙሉ አጠፋ።

- መቅሰፍቱ፥ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 9፡23-26

23- ሙሴ በትሩን ወደ ሰማይ ባነሣ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ነጐድጓድና በረዶ አወረደ፤ መብረቅም በምድሪቱ ላይ ሆነ። እግዚአብሔር በግብፅ ምድር በረዶ አዘነበ።

24- በረዶ ወረደ፤ መብረቅም አብረቀረቀ፤ ግብፅ አገር ከሆነችበት ዘመን አንሥቶ በምድሪቱ ሁሉ እንደዚህ ያለ አስከፊ ማዕበል ሆኖ አያውቅም።

25- በመላው ግብፅ በረዶ በመስክ ላይ ያለውን ሁሉ፣ ሰዎችንና እንስሳትንም መታ፤ በመስክ ላይ የበቀለውን ሁሉ አጠፋ። ዛፉን ሁሉ ባዶ አስቀረ።

26- በረዶ ያልወረደበት ቢኖር እስራኤላውያን የሚኖሩበት የጌሤም ምድር ብቻ ነበር።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በስምንተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የአንበጣዎችን መቅሰፍት ላከ።

- አንበጣዎች የተረፉትን የፈርዖንንና የግብፃውያንን ዛፎችና ሰብሎች በሙሉ

አልሞተም።

7- ፈርዖን ያጣሩ ዘንድ ሰዎች ልኮ ከእስራኤላውያኑ እንስሳት አንድም እንኳን አለመሞቱን ተገነዘበ። ያም ሆኖ ልቡ እንደ ደነደነ ስለ ነበር፣ ሕዝቡን አልለቀቀም።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በስድስተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የእባጭ መቅሰፍት ላከ።
- ፈርዖንና ሁሉም ግብፃውያን በእባጮች ተመቱ።

- መቅሰፍቱ፥ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 9፡10

10- ስለዚህ ከምድጃው ዐመድ ወስደው በፈርዖን ፊት ቆሙ፤ ሙሴም ወደ ሰማይ በተነው፣ መግል የያዘ እባጭም በሰዎችና በእንስሳት ላይ ወጣ።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

• በሰባተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የበረዶ መቅሰፍት ላከ።



- ምክንያቱም ፈርዖን በእግዚአብሔር ለማመን ባለመፈለጉ ነው።
- ምክንያቱም ፈርዖን ኃጢአቱን ስለወደደ ነው።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ በእግዚአብሔር አላመኑም።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ በአገራቸው የሚገኘውን ታላቅ ወንዝ ያመልኩ ነበር።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ ፀሐይን ጨረቃንና ክዋክብትን እንዲሁም ብዙ እንስሳትን ያመልኩ ነበር።

- የግብፅ ሕዝብ ፈርዖንን እንደ አምላክ ያመልክ ነበር።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ያመልኩ ነበር።

- በፈርዖን የአገዛዝ ዘመን ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነቶች አያምኑም ነበር።

- ዛሬም ቢሆን ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር እውነቶች አያምኑም።

- ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነቶች ለማመን ስላልፈለጉ ሰይጣን እንዲያስታቸው እግዚአብሔር ፈቀደ።

- ሰይጣን ሰዎችን ስላሳተ ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው፥ ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ያመልካሉ።

- ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር እውነቶች ለማመን ስላልፈለጉ እግዚአብሔር አብርሃምን የእስራኤላውያን አባት እንዲሆን መረጠው።

- እግዚአብሔር አብርሃምንና እስራኤላውያንን፥ በእነርሱ ዘር በኩል አዳኝ ለመላክ መረጠ።

- እንዲሁም እግዚአብሔር እውነቶቹን በመጽሐፉ ውስጥ ለመጻፍ አብርሃምንና እስራኤላውያንን መረጠ።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል።

- እስራኤላውያን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ ፈርዖን እንደማይፈቅድላቸው እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ከመፈጸሙ አስቀድሞ ያውቃል።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ እምቢ ካለ በኋላ እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን እናድምጥ፡

ዘጸአት 6፡1

1- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «አሁን በፈርዖን ላይ የሚደረገውን ታያለህ፤ ከኀያሉ እጄ የተነሣ እንዲሄዱ ይለቃቸዋል፤ ከኀያሉ እጄ የተነሣ ከአገሩ ያስወጣቸዋል» አለው።

- እግዚአብሔር ለፈርዖንና ለግብፃውያን ታላቅ ኃይሉን ለማሳየት የወሰነው



- በአራተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የዝንብ መንጋ ላከ።

- የፈርዖን ምድርና የግብጻውያን ምድር በዝንብ መንጋ ተወረረ።

- መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 8፡24

24- እግዚአብሔርም እንዲሁ አደረገ፤ አስጨናቂ የዝንብ መንጋ በፈርዖን ቤተ መንግሥትና በሹማምንቶቹ ቤቶች ላይ ወረደ፤ መላው የግብፅ ምድር ከዝንቡ የተነሣ ተበላሽቶ ነበር።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በአምስተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር በእንስሳት ሁሉ ላይ የሞት መቅሰፍት ላከ።

- ሁሉም የፈርዖንና የግብፃውያን ፈረሶች ከብቶች በጐች ግመሎችና አህዮች ሞቱ።

- መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 9፡6-7

6- በማግሥቱም እግዚአብሔር ነገሩን ፈጸመው፤ የግብፃውያን እንስሳት በሙሉ አለቁ፤ ነገር ግን የእስራኤላውያን ከሆኑት እንስሳት አንድም

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በሦስተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር ተናካሽ ትንኞችን ላከ።

- ፈርዖን ግብፃውያን ሁሉና መላው የግብፅ ምድር በተናካሽ ትንኝ ተወረረ።

- መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 8፥16-17

16- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «አሮንን <በትርህን ሰንዝረህ የምድርን ትቢያ ምታ> በለው፤ ከዚያም በግብፅ ምድር ያለው ትቢያ ሁሉ ተናካሽ ትንኝ ይሆናል» አለው።

17- እነርሱም እንዲሁ አደረጉ። አሮን በትሩን እንደ ያዘ እጁን ሲዘረጋና የምድሩን ትቢያ ሲመታ፣ በግብፅ ምድር ያለው ትቢያ ሁሉ ተናካሽ ትንኝ ሆነ፣ ሰውንም ሆነ እንስሳውን ተናካሽ ትንኝ ወረረው።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመ በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።



ለምን ነበር?

- እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንዲያውቁ ነው።

- እግዚአብሔር በአገራቸው ያለው ትልቁ ወንዝ አምላክ አለመሆኑን ለፈርዖንና ለግብፃውያን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- እግዚአብሔር ፀሐይ ጨረቃና ክዋክብት አምላክ አለመሆናቸውን ለፈርዖንና ለግብፃውያን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- እግዚአብሔር ብዙዎቹ እንስሳዎቻቸው አማልክት አለመሆናቸውን ለፈርዖንና ለግብፃውያን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- እግዚአብሔር ለፈርዖንና ለግብጻውያን ፈርዖን አምላክ አለመሆኑን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- ደግሞ ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር አምላካቸው እርሱ መሆኑን ያውቁ ዘንድ ኃይሉን ለማሳየት ወሰነ።

ዘጸአት 6፥2-8

2- እግዚአብሔር ሙሴን አለው፣ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ።

3- ሁሉን የሚችል አምላክ ሆኜ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብ ተገለጥሁላቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር (ያህዌ) በተባለው ስሜ ራሴን አልገለጥሁላቸውም።

4- በእንግድነት የሚኖሩባትን የከነዓንን ምድር እንድሰጣቸው ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ።

5- ደግሞም፣ በግብፃውያን ሥር በባርነት ሆነው ያሰሙትን የእስራኤላውያንን የሥቃይ ድምፅ ሰምቻለሁ፣ ኪዳኔንም አስታውሻለሁ።

6- ስለዚህ፣ ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤ <እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ከግብፃውያን ቀንበር አወጣችኋለሁ። ለእነርሱ ባሪያ ከመሆን ነፃ አወጣችኋለሁ። በተዘረጋች ክንድና በታላቅ ፍርድ እቤዣችኋለሁ።

7- የራሴ ሕዝብ አደርጋችኋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ። ከግብፃውያን ቀንበር ያላቀቅኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላክ መሆኔን ታውቃላችሁ።

8- ከዚያም ለአብርሃም ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ እሰጣችኋለሁ ብዬ ወደ ማልሁላቸው ምድር አመጣችኋለሁ። ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ። እኔ እግዚአብሔር ነኝ።»

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን እርሱ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ መሆኑን ያውቁ ዘንድ ኃይሉን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- እግዚአብሔር እርስ የእስራኤላውያን አምላክ መሆኑን ያውቁ ዘንድ ኃይሉን ለእስራኤላውያን ሊያሳያቸው ወሰነ።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ሊለቅ ስላልፈለገ እግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉን ማሳየት ጀመረ።

- እግዚአብሔር ለግብፃውያንና ለእስራኤላውያን ታላቅ ኃይሉን ያሳየው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ታላቅ መቅሰፍት በማውረድ ነበር።

- በመጀመሪያው መቅሰፍት እግዚአብሔር ታላቁን የግብጽ ወንዝ ውኃ ወደ ደምነት ለወጠው።

- መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 7፡20-21



20- ሙሴና አሮን እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ። አሮንም በንጉሡና በሹማምንቱ ፊት በትሩን አንሥቶ የዐባይን ወንዝ ውኃ መታ። ውኃውም በሙሉ ወደ ደም ተለወጠ።

21- በዐባይ ያሉት ዓሦች ሞቱ፣ ወንዙም ከመከርፋቱ የተነሣ ግብፃውያኑ ውኃውን ሊጠጡት አልቻሉም። በግብፅ ምድር ሁሉ ደም ነበር።

- ፈርዖን ሙሴ መቅሰፍቱን እንዲያስቆምለት ለመነው እርሱም እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተስማማ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ካቆመው በኋላ ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም አለ።

- በሁለተኛው መቅሰፍት እግዚአብሔር የእንቁራሪት መቅሰፍት ላከ።

- የፈርዖንና የግብፃውያን መሬት በሙሉ በእንቁራሪት ተሸፈነ።

- መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ግን አልገባም።

ዘጸአት 8፡5-6

5- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን አለው፣ «አሮንን፣ <በትርህን ይዘህ በምንጮች፣ በቦዮችና በኩሬዎች ላይ እጅህን ዘርጋ። ጓጉንቸሮችም በግብፅ ምድር ላይ እንዲወጡ አድርግ> በለው።»

6- አሮንም በግብፅ ውሆች ላይ እጁን ዘረጋ፤ ጓጉንቸሮችም ወጥተው ምድሪቱን ሸፈኑ።